ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የተከበሩ አባታችን ሊቀሊቃውንት ወርቅነህ ኃይሌ የተከበራችሁ አባቶች ካህናት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ወንድሞች ዲያቆናትና ወጣት የሰንበት ት/ቤት አባላት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ውበቷና ጌጧ የካህናት መርኩዝና ረዳት የየአጥብያው አብያተ ክርስቲያናት ተወካይ ምእመናን ልዑል እግዚአብሔር በረድኤት ጠብቆ በሐብት አክብሮ በዚህ ዓይነት እንድንገናኝ ስለፈቀደ እናመሰግነዋለን፡፡እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡

*«ኢትክል ተከብቶ ሀገር እንተ ተሐንፀት መልዕልተ ደብር» ማቴ 5፡-14*

ስለቤተ ክርስቲያናችን በአጭሩ ጥቅሱ እንደሚያመለክተው በውነት በፍቅርና በአንድነት መሠረትነት ላይ ስለታነጸች ከኢትዮጵያውያንም አልፎ የዓለም አቀፉን ኅብረተ ሰብ ተኩረት እየሳበች የአለች ናት፡፡የእውቅናውም ምንጭ

ሀ. በመንፈሳዊ አገልግሎቷ
ለ. በአስተዳደራዊ መዋቅሯ
ሐ. የበጎ አድራጎት ሥርዋ
መ. የአስተባባሪነት ጥረቷ

## መንፈሳዊ አገልገሎት

ቤተ ክርስቲያናችን ከዓመት እስከ ዓመት በእየቀናቱ ከ16 ሰዓት በላይ ለምእመናን ክፍት በመሆኑ ሙሉ ቀን በአለማቋረጥ በየአቅጫው እየመጣ ሕዝበ ክርስቲያኑ አምልኮቱን ይፈጽማል፡፡ ዓርብና እረቡዕ የስብከተ ወንጌል ትምህርት የካሔዳል፡፡ ሳምንቱን ሙሉ የምክር አገልገሎት ይሰጣል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በሳምንት ውስጥ ከ2500 - 3500 በላይ ምእመናን ይሳተፋሉ፡፡የሰዓታት የማኅሌት የቅዳሴና የነግህ ጸሎት አስፈላጊ በሆኑ ቀናት ሁሉ ይከናውናል፡፡አገልጋዮቿ ካህናት ልዩ ልዩ የፀጋ ስጦታ የታደሉ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በአሳለፍነው ዓመት እንካን ቅዱስ ያሬድን በማስታዋወቅ ደረጃ በርከታ ያሬዳዊ መርሐ ግብሮች ተካሂደዋል፡፡የቤተ ክርስቲያናችን የመንፈሳዊው ክፍል ኃላፊ የሆኑት ሊቀ መዘምራን ሞገስ ሥዩም በአላቸው ሙያና አገልገሎት ዓለም አቀፍ ሽልማት በማግኘታቸው ቤተ ክርስቲያናችንንም ዓለም አቀፍዊት አድርገዋታል፡፡

በዓመት አራት ጊዜ ታትሞ የሚወጣ እማሬ መጽሔት እንደ አስፈላጊነቱ እየታየ «ዜና ደብረ ሰላም» በሚል ርዕስ የቤተ ክርስተያናችንን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ኒውስ ሌተር ይወጣል፡፡ የኢትዮጵያን ዘመን መለወጫ ምክንያት በማድረግ የኢትዮጵያውያን ምሁራን የሚያሳትፍ እውቅ ሰባክያንንና መዘምራንን የአቀፈ በርካታ ምዕመናን የሚታደሙበት ልዩ ጉባዔ ይካሄዳል፡ እንዲሁም በየዓመቱ የቅዱስ ያሬድ በዓል ሲከበር እነሆ አሥር ዓመቱን አስቆጥሯል፡፡ መንፈሳዊ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን የሚመለከትና የሚወስን የካህናት ጉባዔ አለ፡፡

## አመሠራረትንና አስተዳደር

ቤተ ክርስቲያኗ ህጋዊ እውቅናን ሳታገኝ የዲቁና ማዕርግ በነበራቸው የዛሬው መጋቤ ካህናት ከሃሊ ወንደአፈረውና ለሃይማኖታቸው ቀናኢ በነበሩ ወንድሞችና እህቶች መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሲያካሄድ ቆይቶ በ1987 ዓ.ም ህጋዊነት አግኝቶ

ተመሠረተ፡፡ውሱን በሆኑ አገልጋዮች በኪራይ ቤት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ በ1997 ዓ.ም ይህ የአለንበት በ455000.00 ሲገዛ በ1998 ዓ.ም በ16000.00 መኪና ማቆሚያው ቦታ ተገዛ፡፡በ2001 የካህናት ማረፍያ ተብሎ ዛሬ ተከራይቶ ገቢ የሚያስገባውን በ26000.00 ሲገዛ በ2003 ዓ.ም ደግሞ ኩታ ገጠም የሆነውን በ1270000.00 ተገዝቶ የሚበልጠው እዳው ተከፍሎ ቀሪውን ለመፈጸም ጥረት እየተደረገ በሌላ በኩል ደግሞ አዲሱን ህንፃ ለመጀመር ቅደመ ዝግጅት እየተከሄደ ነው፡፡ በመዝገብ ላይ የሠፈሩ አባላት ከ2000 በላይ ሲሆኑ ቋሚ ሆነው ግዴታቸውን የሚወጡ በመብታቸው የሚጠቀሙ ከ1000 የአነሱ አባለት የአሉ ሲሆን እነዚሀ ጠቅላላ ጉባኤ ይባላሉ ከነዚህ ውስጥ 12ቱ የቦርድ አባላት እነሱን በመወከል አመራሩን ያካሄዳሉ በአለቃው የሚመራ የዕለት ከዕለት ተግባገሩን የሚያከናውን የአስተዳደር ጉባኤ አለ፡፡

## *በጎ አድራጎትን በተመለከተ*

የቤተ ክርስቲያናችን ዓላማ ገና ከጅምሩ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጎን የበጎ አድራጎት ሥራን ስለሚያካትት ከተመሠረተበት ጌዜ ጀምሮ የበጎ አድራጎት ሥራዎች በአለማቋረጥ ያካሄዳል በተለይም በ2000 ዓ.ም በሀገራችን ሕዝባችን በርሃብ በተመታበት ወቅት በገዳመ ተክለ ሃይማኖት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አማካይነት ጥሪውን ሲያስተላልፍ የመጀመርያው ስብሰባ የተደረገው የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴም የተቋቋመውና ጽ/ቤቱም በዚሁ ቤተ ክርስቲያን በነፃ በተሰጠው ቦታ ላይ ነው፡፡ የሂሳብ ሪፖርቱም እንደሚያመለክተውም የሚበልጠው ገንዘብ ከዚህ ቤተ ክርስቲያን የተዋጣ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በሀገራችን በቤተ ክርስቲያናችንና በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ በአክራሪ የእስልማና ተከታዮች በደረሰውም ጭፍጨፋ ግንባር ቀደም በመሆን ለሞቱት ጸሎተ ፍትሐት በሕይወት ላሉት የምኅላ ጸሎት ከማድረስ ጋር ድረጊቱን በመኮነን መንግሥት ኃላፊነቱን እንዲወጣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንም የሚያነቃ መግለጫ አስተላልፋል፡፡ ሕዝበ ክርስቲያኑን እያስተባበር ከሚያዋጠው ገንዘብ ውጪ ለበጎ አድራጎት በጀት በመያዝ ለአብነት ት/ቤቶች እዚህም ሀገር ረዳት ሳይኖረው በድንገት ሲታመሙ ሲሞቱ እርዳታ ያደርጋል እንዲሁም በህጋዊነትም ሆነ ህገ ወጥ ወደዚህ ሀገር ሲገቡ ተቀባይ ረዳት የሌላቸውን እየተቀበለ የሚያስተናግዳቸው ብዙዎች ናቸው፡፡እንዲሁም ዛሬም በሀገራችን በሚልዮን የሚቆጠሩ የወገኖቻችን መራብ እንደተሰማ የባለ አደራው ቦርድ አስቸካይ ሰብሰባ በማድረግ ከጳጉሜን 5 ቀን 2000 ጀምሮ አስከ መስከረም 4 ቀን 2001 በነበረው የምሽት ጉባኤና የቅዱስ ያሬድ በዓል የተከበረበትን የእሁድ ዕለት ገቢ በጠቅላላው በድርቅ ለተጎዳው እንዲውል ወስኗል ቤተ ክርስቲያናችን ምን ያህል ከሁሉም በላይ ቅድምያ የምትሰጠው ለበጎ አድራጎት ሥራ እንደሆነ ድርጊቱ ያረጋግጣል፡፡

## *የአስተባበሪነትን ሥራ በተመለከተ*

በዚህ ዋሽንግቶን ዲሲ አካባቢ ምዕመናኑም ሆኑ ካህናቱ ከአንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው በመሄድ ማገልገልም ሆነ መገልገል የማይቻልበት መለያየት የሰፈነበትን አካባቢ በጋራ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በአካባቢው እንዲሰፍን በማድረግ እንዲሁም የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያስተባበር ተጠሪነቱን ለካህናት አባቶች የአደረገ በካህን የሚመራ በጻድቁ በአቡነ ተክለ ሃይማኖትና ገዳማቸውን በሚያስታውስ«ገዳመ ተክለ ሃይማኖት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1995 ዓ.ም እንዲቋቋም ሲሆን እንዲሁም በ2002 ዓ.ም «ማኅበረ ካህናት» ተቋቋመ በማኅበራቱም አማካይነት በተደጋጋሚ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስብሰበዎች ተደረገዋል የዚህ ሁሉ መነሻና መድረሻ የርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ሀገር የወቀው ፀሐይ የሞቀው ስልሆነ በአጭሩ የአስተባባሪነት ሥራዋ ይህን ይመስላል፡፡ ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን በአጭሩ ይህን ያህል ከአወቅን ከገለጽኩ ቤተ ክርስቲያናችንም ሆነች ሀገራችን በፈታኝ ሁኔታ ላይ በአሉበት በዚህ ዘመን የአለነ ካህናትም ሆን ማኅብረ

ምዕመናን ሚዛን ላይ የሆንበት ገዜ በመሆኑ ለጉባኤው የግሌን ኃሣብ እንዳቀርብ እንድገልጽ ይፈቀድልኝ።

## እራስን ከታሪክ ወቀሳ ከህዝብ ቁጣ ለማዳን ትውልድን ከጥፋት ለመታደግ ይህ ጉባዔ ምን ይጠበቅበታል?

በዘመነ አበው ዮሴፍ በስደት በምድረ ግብጽ በነበረበት ወቅት በርካታ የመከራውን ገፈት በትዕግሥት አሳልፎ በእምነቱ ጸንቶ ለሥልጣን ሲበቃ ለወገኖቹ ችግር መድረሱ

ዜዋዌ ሆኖ እስራኤል በስደት በነበሩበት ወቅት እምነታቸውን የሚፈትን ጥያቄ ሲጠየቁ « ውስተአፍለገ ባቢሎን ህየ ነበርነ ወበከይነ ሶበ ተዘከርናሃ ለጽዮን። ውስተ ኲሐቲሃ ሰቀልነ ዕንዚራቲነ ። እሰመ በህየ ተስእሉነ እለ ዔወዉነ ነገረ ማኅለት።ወእለሂ ይወስዱነ ይቤሉነ ኀልዩ ለነ እመ ኃልይሃ ለጽዮን።እፎ ነኀሊ ማኅሌተ እግዚአብሔር በምድር ነኪር። እመሰ ረሳዕኩኪ ኢየሩሳሌም ለትርስዐኒ የማንየ። ወይጥጋእ ልሳንየ በጉርዔ ለእመ ኢተዘከርኩኪ። በማለት በእንባ ጸሎታቸውን ያደርሱ እንደነበር በእምነታቸው እንደጸኑ ለባዕዳን አማልክት እራሳቸውን እንዳላበረከቱ ሀገራቸውን እንዴት አድርገው እንደሚወዱ እምነታቸውንና በህላቸውን ምን ያህል ጠብቀው እንደተጓዙ መዝሙሩ ያረጋግጣል። መዝ 136፡-1 በምርኮ የነበረው ነህምያ« እኔም አኛም የአለንበት ጉስቁልና ኢየሩሳሌም እንደፈረሰች በሮቿ በእሳት እንደተቃጠሉ ታያላችሁ አሁንም ከእነግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን ኑ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ»ነህ 2፡-17 ሲጸልይ «አምላከችን ሆይ ተንቀናልና ሰማ» ነህ 4፡-14 ወታደራዊውንና ፖሊተካዊ እርምጃ ሲወስድ ደግሞ «አትፍሩ ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ ስለወንድሞቻችሁና ስለሀገራችሁ ተዋጉ» ነህ 4፡-15 በማለት የኢየሩሳሌምን ቅጽር ሲገነባ ህዝቡን ሲያጠናክርና ሲያነሳሳ ካህናቱና ነቢያቱ ደግሞ ህዝቡን «ወደ ንስሐ ተመለሱ ንስሐ ግቡ ልባችሁን በመንገዳችሁ አድርጉ»በማለት ሕዝቡን ለንስሐ ሲያዘጋጁ ለፖሊቲካ መሪዎች ደግሞ«በመንፈሱ እንጂ በኃይልና በብረታት እንደማይሆን በማስረዳት መንጋውን በትክክል ለማያሰማሩ ካህናት ደግሞ «መንጋውን ለሚተው ለምናምንቴ እረኛ ወዮለት ሰይፍ በክንዱና በቀኝ ዓይኑ ይሆናል ክንዱም አጥብቃ ትደቃለች ቀኝ ዓይኑም ፈጽማ ትጨልማለች» ዘካ 11፡-17
ትንቢታዊና ትምሕርታዊ ተገሣጽ ሳይቀር በመስጠት ካህናቱ ሕዝቡን በመምከርና በማስተማር ሕዝቡም ትምህረቱን በእንባ ጭምር በመቀበል ካህናቱ ነቢያቱ ሕዝቡ መሪዎቹ ሳይቀር አንድ ሆነው በአንድ ኃሣብ ስለተጓዙ ለሚጠት እብደበቁ የእስራል ታሪክ ያረጋግጣል።

የእስራኤልን ታሪክ በዚህ ዓይነት ስነመለከተው የሀገራችንን ታሪከ ደግሞ አፄ ካሌብ የነግራንን ክርስቲያናች ሲታደጉ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ አድዋ ላይ ጠላትን ድባቅ ሲመቱ ያን ለማድረግ ያስቻላቸው ምን ኃይል ነበር? በምን እንደሆነ እዚህ የአለው ሁሉ የታሪኩ በለቤት ስለሆነ ጊዜ ላለማጥፋት ለእንናተው ትቸዋለሁ።

ቅዱሳን አባቶቻችን እነአቡነ ኢሱስ ሞዓ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዛጓና በሰሎሞናዊው የሥልጣን ለእኔ ይገባኛል የተነሳ የውጪ ጠላት ሳይመጣ በሥልጣን የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎራ አበጅቶ ሲተላለቅ ሲጠፋፋ ዝም በለው ሳይመለከቱ በመሐል በመግባት በመምከር በመስተማርና በመጸለይ የፀብ ጎራውን አፍርሰው የእርቅ መሠረት ጥለው የይቅርታ ግርግርዳ ገንብተው የፍቅር ጣርያ አልብሰው ሁሉም ተሳስቦ በአንድነት የሚኖርባት ኢትዮጵያን ያስተላለፉልን ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ ሳይሉ «ዘይፈቅድ የትለወኒ ይጽላ ነፍሶ ወያጥብዕ ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ ወይትለወኒ ወዘይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ለይግድፋ ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንትአየ የረክባ ወምንተ ይበቁዖ ለሰብእ ለእመ ኩሉ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ሐጉለ ወምንተ እምወሐበ ሰብእ ቤዛሃ ለነፍሱ» ያለውን

አምላካዊ መመርያ ተግባራዊ በማድረግ በመኀዛቸው ነበር ያን የጥባትና የማስታረቅ መንፈስ ያገኙት ማቴ 16:24-27::

ለምሳሌ ያህል የሌላ ኅብረተ ሰብ ታሪክ ላወሳ እወዳለሁ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን በደቡብ አሚሪካ ማለትም በአረጀኒቲና በፔሩ በኮሎቢያ በመክሲኮና በመሳሰሉት ሀገሮች የፊውዳሉ ሥርዓት የሰፈነበት ካፒታሊዝም ብቅ ብቅ የአለበት  ዝቅተኛውና ገበሬው የሚጨቆንበት የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅብር በአውሮፓ እራሱን ቀና በማድረግ ምድራዊ ገነት የሚያጎናጽፍ የወዝ አደር አባገነንነት የበላይነት የሚያሰፍን እግዚአብሔር የለሽ ጽንስ ኃሣብ አንግቦ በነዚህ ሀገሮች እንቅስቃሴ የጀመረበትም ነበር በደቡብ አሜሪካ አብዛኛው የሮማ ካቶሊካዊት እምነት ተከታይ በመሆኑ የኮሚኒስቱን ሥርዓተ ማኅበር በአይዲዎለጂው ምክንያት የተነሳ ለመቀበል ግራ የተጋባበት ወቅት ነበር በዚህ በቀውጢ ጊዜ ነው ካህናቱ ግንባር ፈጥረው ዓለማቸውን ቀርጸው ክርስትውን እንደያዘ በተቸገረውና በዝቅተኛው ሕዝብ መካከል በመግባት የተራበውን በማብላት የታረዘውን በማልበስ ልጆቻቸው ትምህርት እንዲያገኙ በማድረግ በፍቅር ላይ የተመሠረተ የበጎ አድራጎት በማቋቋም ለኅብረተ ሰቡ እንደ ደረሱለትና  ትክክለኛ ፍርድ እንዲመጣ ሰላም ፍቅር በሕዝብ መካከል እንዲሰፍን በማድረግ «LIBRATION ThEOLGY> በሚል መርሆ ትልቅ ሥራ እንደሠሩ ማኅደረ ታሪካቸው ይጠቁማል::

እንዲሁም < I have a dream> ብሎ የተነሣው ዛሬ እኛ በዚህ ክፍለ ዓለም በነፃነት እንድንኖርና ጥቁር ነጩ ቤተ መንግሥት ለመግባት በር የከፈተ  ለዚህ የአበቃ ካህኑ ማርቲን ሉተር ኪንግ እንደሆነ ሥራው በተግባር እየተፈጸመ ነው::

በአውሮፓም በ1956 ዓ.ም በሀንጋሪ 1968 ዓ.ም በቸኮዝላቢያ የኮሚኒስቱን ሥርዓተ ማኅበር በመቃወም በካህናቱ አስተባባሪነት ተደርጎ እንደነበርና በሶቤት ኅብረት አባገነኑ የኮሚኒስቱ መንግሥት አማካይነት እንደከሸፈና እንደገና  ቀደም ሲል በ1981 ዓ.ም በፖላንድ ዘገየት ብሎ 1989 ዓ.ም ደግሞ በሀንጋሪ በሩማንያ በቸኮዝላቢያ በአጠቃላይ በምሥራቅ አውሮፓ እንቅስቃሴው እንዲፋፋም የበርሌን ግንብ እንዲፈርስ ለረዥም ጊዜ ተለያይቶ የነበረው ሕዝብ እንዲገናኝ ያደረገ ታላቁ የሶበት ኅብረት መደርመስ መፈራረስ መነሻውም መድረሻውም የካህናቱ ግንበር ቀደም እንቅስቃሴ እንደነበረ በወቅቱ በቦታው ስለነበርኩ ዓይን ምሥክርነቴን እሰጣለሁ::በርካታ ተመሳሳይ ምሥክሮችን በአቀረበረኩ ነበር ነገር ግን « እሰመ ኅፁር ዕለትየ» ነውና

ከመጽሐፍ ቅዱስ የእስራኤልን ከታሪካችን የነገሥታቱን ከገድላችን የቅዱሳን አባቶች የውጫውንም ዓለም የካህናትንና የምእመናንን እንቅስቃሴ መነሻና መድረሻ ውጤታማነቱንም ተመልክተናል::

## በእኛ ዘመን የተፈጸሙና እየተፈጸሙ የአሉ መዘክራዊ መጠይቅ

እኛስ በሀገራችን እግዚአብሔር የለሽ አይዲዎሎጂ የሚያራምድ መንግሥት አልተቋቋመም? በነጭና በቀይ ሽብር ምክንያት ወጣቱ እንደ ቅጣል አረገፍምን? ሀገሪቱን ይመሩ የነበር ያለ ፍርድ ከስድሳ የሚበልጡ በአንድ ጉድጓድ አልተቀበሩምን? ንጉሠ ነገሥቱስ አሰከሬናቸው በሽንት ቤት አልተጣለም? የቤተ ክርስቲያኒቱ እራስ ቅዱስ ፓትርያሪኩ ያለፍርድና የአለአግባብ አልተረሸኑም?ለዘመናት አሐቲነቷን ጠብቃ የኖረች ቤተ ክርስቲያናችን በእኛ ዘመን አልተከፈለችም? ሀገራችንስ ወደብና እራስ አልባ አልሆነችምን?ካህናቱ በቤተ መቅደሱ እንደ ፋሲካ ጠቦት አልታረዱም(አልተሰዉም) አብያተ ክርስቲያናት በእሳት አልጋዩም ምዕመናን ቤታቸው ተቃጥሎ ንብረታቸው ወድሞ ወንጅል እንደፈጸሙና እንደ ባእዳን ከቀያቸው አልተባረሩም?ህዝባችን በረኀብ በእርዛት በበሽታ አልተሰቃየም አሁንስ አይሰቃይም? ፍትሕ በማጣት እግሩ እንደ መራው ሲኀዝ አውሬ የበላው በየባሕሩ ጠልቆ የቀረው የደረሰበት ያልታወቀው በሕይወት ተርፎ በደረሰበት ሀገር እንግልት ሥቃይ መከራ የማይደርስበት

ማነው?በሀገሪቱ ሰላም መረጋጋት በአለመኖሩ ገበሬው አርሶ እንዳያዘምር ነጋዴው ነግዶ እንደያተረፍ ሠራተኛው በሙያው በችሎታው ሠርቶ ውጤታማ እንዳይሆን አልተደረገም? .. ..ወዘ

በአለንበት ክፍለ ዓለምስ ምእመናን እምነታቸውን ሊጠብቁበት ምግባራቸውን ሊያጸኑበት የአምልኮት ሥፍራ ሲያዘጋጁ አንዳድ እራስ ወዳድ ካህናት በውድም ሆነ በግድ አንባ ገነን በመሆን  ገንዘብ አላባከኑም? መዕመናን አለሳዘኑም? እነርሱን በትነው በገንዘቡ ሹመት አልገበዩበትም? አምባ ገነኑ ምዕመን ደግሞ ለርካሽ ፖለቲካው እንዲያመቸው በሃይማኖት ስም በሕዝብ ንብረት ቤተ ክርስቲያን የግል ፖለቲካ ማካሄጃ አላደረጉትም? ካህናት ያለምንም ጥፋት ደሞዛቸውን ተነጥቀው አልተባረሩም?

እኔ የጳውሎስ እኔ የአጵሎስ በመባባል ወንድም ከወንድሙ አልተቆራረጠም? ምዕመናኑ ከካህናቱ አልተፋጁም? በየፍርድ ቤቱ አልተንከራተቱም? እንዲሁም« ማኅበረ ምዕናን ዘተዋኅዶ» ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን» ማኅበረ ካህናት» ዓለም አቀፍ የምዕመናን ጉባዔ»በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ግለሰቦች አነሳሽነት አልተቋቋሙም?ጊዜ አልጠፋባቸውም? ገንዘብ አልፈሰሰባቸውም? የሰዎች አእምሮ አልተጨመቀባቸውም? ዘሬ የት ነው የአሉት? የቀረቡት ጥያቄዎች ሁላችንም የአለፍንባቸውና የምናውቃቸው በመሆኑ መልሱን መልሰን« ቦ ዘምእት» በሚለው ውስጥ እንደምንታደም ባረጋግጥም የቤተ ከርስቲያናችን መከፈል ሀገራችን በእርገቷ  በብልጽግንዋ ዘርፍ የዓለም ጅራት በረኀቡ በበሽታ በድህነቱ የመጀመርያዋ እንድትሆን መደረክ አዘጋጅተን ተዋንያኑ ባንሆንም እንካን ተመልካቾች ሆነናልና በዚህ ዘመን የአለን  ትልቁም ትንሹም ወንዱም ሴቱም ካህኑም ምዕመኑም  ከተጠያቂነት  አናመልጥምና የታሪካችን ጠባሳ ምን ያህል ይሰፋ? የሚለውን  ጉባኤውን ስጠይቅ ጠባሰውን ለማጥበብ ቤተ ክርስቲያናችንን ሀገራችንና ሕዝባችንን ለመታደግ ከእኛ በዚህ ዘመን ምን ይጠበቃል? በማለት በድጋሜ እጠይቅና የእኔን ድርሻ እንደ ሚከተለው አቀርባለሁ::

1. «ከማሁ ይብራ ብርሃንክሙ በቅደመ ሰብእ ከመ ይርአዩ ምግባሪክሙ ሠናየ»የአለውን አምላካዊ ቃል መሪ በማደረግ ከቃላት መደርደር ከንግግር ማሳመር ተላቆ ወደ ተግባር መሸጋገር በዚህ ገጸ ንባብ «ምግባሪከሙ»አለ እንጂ ቃልክሙ አላለምና በእኛ ኅብረተ ሰብእ ማኅበራትም ሆኑ ድርጅቶች ልምሾ እየሆኑ የሚቀሩት ተግባራዊነት ስለሚጎላቸው እንደሆነ ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልገው አይደለም ለተግባራዊነት መስዋትነት ያስፈልገዋል ያለመስዋዕትነት ተግባራዊነት የአለ ተግባራዊነት መስዋዕትነት የለምና::
   ተግባራዊነትን የሚከታትል ቢኖር

2. ከጠባብነት መጠላላት ከመጠላላት መለያየት ከመለያየት መጠፋፈት ከመጠፋፋት የሚከተለው አለመኖር ነውና ወደ አለመኖር ከመድረሳችን በፊት የአባቶቻችን የቅዱሱን የአባ ኢየሱስ ሞዓንና የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዱካቸውን በመከተል በአሁኑ ጊዜ የሀገራችንም ሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ችግር መሠረቱ መነሻውና መድረሻው ከጠባብነት የመነጨ መለየያት ስለሆነ «ሳይቃጠል.. ..» እንደሚባለው የመጀመርያው ሥራችን የተለያዩ አባቶችን በማቀራረብ «የብፁዓን ገባርያነ ሰላምን» ተግባር መፈጸምና ማስፈጸም ይሆናል::
   ለዚህ አንድ ግብረ ኃይል መሰየም:

3. ረዐይኬ አባግዕየ ረዐይኬ መሐስእየ ረዐይኬ አባግዕትየ» በጎችን ጠቦቶችንና ግልገሎችን የማሰማራትና የመጠበቅ ኃለፊነት ለጊዜው ለቅዱስ ጴጥሮስ ቢሰጠው ፍጻሜው ግን ዛሬ በዚህ ዘመን ለአለነው ለእኛ ነውና ዛሬ ለሀገራችን  ለሕዝባችን ለተተኪው ትውልድ እዳ አለብን በችግሩ ሁሉ ልንደርስለት እግዚአብሔር ሁሉን አሟልቶ ነፃነት በአለበት  ቦታ አስቀምጦናልና የትምህርትንና የበጎ አድራጉትን

*ሥራ ማጠናከር ይጠበቅብናል። ምንአልባት የሀገርን መዋረድ የሕዝብን ጉስቁልና የቤተ ክርስቲያናችንን መነቀፍ ጉዳይ አንስተን ስንነጋገር ነገሩ ሳይገባቸው በየዋኀነት እንዲሁም ነገሩ ገብቶቸው ለማደናገር የእነሱን ማንነት ለመሸፈን ፖለቲካ ይናገራሉ የሚሉ እንደማይታጡ እርግጠኛ ነኝ። በሁሉም ዘርፍ እራሱን መስዋዕት አድርጎ የሚቀርብ ጠፋ እንጂ ውነተኛ የሃይማኖት መሪ ፖለቲከኛ ውነተኛ የፖለቲካ መሪ ሃይማኖተኛ መሆኑን የፖለቲካ ሳይንስም ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጣሉ በሚሰነዘረው ሁሉ ሳይሸበሩ መጽናት ያስፈልጋል ።*

4. *የተወሰኑትንም ሆነ የሚወሰኑትን ለመተግበር እቅድና ዓላማን እውን አድርጎ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የገንዘብ ምንጭ ያስፈልጋል ምንጭ ሲኖር ብቻ ነው የማያቋርጥ ፈሳሽ ሊኖር ሚችለው በዚህ ላይ ሁሉም አበክሮ ሊያስብነት ይገባል።*

5. *«ወብየ ካልኣትኒ አባግዕ እለ ኢኮና እምዝንቱ ዐፀድ.. ..»እንደተባለው በቅድምያ በዚህ ኅብረት ያልተካተቱ የእኛን አብያተ ክርስቲያናት የኅብረቱ አካል ማድረግ እንዲሁም በየአካባቢያችን ከአሉት ሃይማኖታዊ ድረጅቶች ጋር ማኅበራዊና ዓለም አቀፍ በሆኑ ጉዳዮች ግንኙነት መፍጠር አብሮ መሥራት የሚቻልበትን መቀየስ እቅድ ማውጣት ያስፈልጋል ብየ እገምታለሁ። በተለይ በሁሉም የሙያ ዘርፍ ምሁራንን ማሰባሰብ የዓላማችን ግብ መምታት ዋንኛ ቁልፍ ነው እላለሁ።*

## ***<u>በመጨረሻም</u>***

*በነህምያ ንግግር ጎሣቤን አጠቃልላለሁ «እኛ የአለንበት ጉስቁልና ኢየሩሳሌም እንደፈረሰች በሮቿም በእሳት እንደተቃጠሉ ታያላችሁ አሁንም ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን የኢሩሳሌምን ቅጽሮች እንሥራ»ነህ 2፡-17 ዛሬ ሀገራችን ቤተ ክርስቲያናችንና ሕዝባችን በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ስለአሉ ካህናቱ የዘመኑ ሐጌዎችና እዝራዎች ምእመናኑ ነህምያዎች በመሆን ሀገራችንን ሕዝባችንና ቤተ ክርስቲያናችንን ከመሳለቂያነት የመታደግ ችሎታውም ዕድሉም ኃይሉም በእጃችን ነው።« የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ባርያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን»ነህ 2፡-20 ብለን ቆርጠን እንነሳ በውነት እንቁም ውነት ነፃ የአደርገናልና።አሜን*

«ወስብሐት ለእግዚአብሔር»

***ሊ/ማ/ዶ/ር አማረ ካሣዬ***